# ከአለንበት አጣብቂኝ ለመውጣት ምን እናድርግ?

ህዝባችን ትግሉን አላቆመም። ያለው የአመራር፤ የአቅጣጫ ሰጭ የአቀነባባሪ ችግር ነው። በዚህ የአመራር ማጣት ጉዳይ ከግንቦት ወር ጀምሮ የለውን ሁኔታ ስንመለከት አን-ድ ቁም ነገር እንታዘባለን። ሚያዝያ ሰላሳ 1997 በቅንጅት ከተጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ወዲህ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ህዝባችንን (ከጥሩምባ መንፋቱና ከሶስቱ ቀን የስራ ማቆም አድማ በስተቀር) ሰላማዊ ሰልፍ ወጥቶም ሆነ በሌላ ሰላማዊ ዘዴ ተቃውሞውን እንዲያሰማ በተቃዋም ድርጅቶች በኩል በይፋ የተጠራ አንድም እርምጃ የለም። ሆኖም ህዝባችን ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለቁጥር የሚታክቱ የተቃውሞ እ-ርምጃዎች ወስዱዋል። ብዙ መስዋእትነት የተከፈለባቸው ሰላማዊ ሰልፎች፤ ስራ ማቆም አድማዎች፤ ወዘተ የህዝብ ቁጣና የወያኔ ትንኮሳ እየተጋገዙ የጋበዙዋቸው ግብታዊ ተጋድሎዎች እንጂ በተቃዋሚ ድርጅቶች ጥሪ የተቀሰቀሱና የተመሩ አይደሉም። እነዚህ ህዝባዊ ተጋድሎዎች ከድርጅቶች አመራርና አነሳሽነት ውጭ ተካሂደዋል። አሁንም እየተካሄዱ ናቸው። ወደፊትም እንደሚቀጥሉ መጠርጠር አይቻልም። ነገር ግን የተደረገውም ሆነ በመደረግ ላይ ያለው የህዝብ መስዋእትነት ፍሬያማ እንዲሆን ከተፈለገ የግድ የፖለቲካ አመራር ያስፈገዋል። ያለውን አደገኛ የአመራር ክፍተት እነዚህን ህዝቡ በግብታዊነት እየተነሳሳ ያለአንዳች መመሪያ የሚያካሂዳቸውን ትግሎች አቅጣጫና ተጨባጭ መፈክር ማስጨበጥና ማቀነባበር የወቅቱ ዋናና አንገብጋቢ ተግባር አድርገን መውሰድ ይኖርብናል። ይህ ካልተደረገ ትግሉን የሚጠብቀው ችግርና አደጋ ግልፅ ነው። ፍሬው የማይታይ መስ-ዋእትነት መሰላቸት የማምጣት አደጋ ከመጋበዙ በላይ ትግሉ ያልተደራጀና ያልተጋገዘ ትግል እንደመሆኑ መጠን ይዋል ይደር እንጂ የተደራጀው የወያኔ/ኢህአዴግ ሃይል ሊያከሽፈው ይችላል። ከዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት ከተፈለገ ለዚህ ህዝባዊ ተጋድሎ አመራር ሰጥቶ ትግሉን ለድል ለማብቃት በሁለት አ)ጣጫ መንቀሳቀስ የግ-ድ ይሆናል። (ይህንን አይነቱን አመራር ማን ይሰጠው በሚለው ጥያቄ ስላለው ክሪዝ ዝቅ ብለን እንመጣለን ስላለው ክፍተት። መጀመሪያ ግን አመራር ስንል ምን ማለታችን ነው???) አመራር ስንል ሁለት ነገሮችን ለመጠቆም ነው። አንደኛ በያለበት ተራ በተራና በግብታዊነት የሚንቀሳቀሰውን ትግል በአንድነት እንዲካሄድ መጣር ማለት ነው። ይህ ደግሞ አመራር እሰጣለሁ የሚለው ሃይል የሚያነሳውን የትግል መፈክር ይመለከታል። በዚህ አሸባሪ አገዛዝ ላይ ብሶት ያለው ሁሉ በትግል ላይ ካለው ወጣቱና ዴሞክራት ጋር በአንድነት እንዲነሳ ልጆቻቸው የጠፉባቸው ወላጆች፤ ከስራ የተባረሩ ሰራተኞች፤ ነግዳቸው የታሸገባቸው ነጋዴዎች፤ ብሶታቸውን አንግበው በሌላ በኩል ደግሞ ሰብአዊ መብቶች ይከበሩ፤ ተጠያቂነት ይኑር፤ ነፃው ፕሬስ መታፈን ይብቃ፤ የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ....ወዘተ እያሉ በውጭም በውስጥም የህዝብን ብሶት የሚያስተጋቡ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች ሁሉ በአንድነት እንዲንቀሳቀሱ መጥራት ያስፈልጋል። ይህ እስካሁን ሲሞከር ቆይቱዋል። በህብረታችን ደረጃ እንኩዋን ደግመን ደጋግመን "የትግል አንድነት ጥሪ" "እስቸኩዋይ ጥሪ" ወዘተ እያልን ብዙ መግለጫዎች አውጥተናል፤ ብዙ ገለጣዎች አድርገናል። ነገር ግን እስካሁን እንደሚታየው ከሆነ እንኩዋን ከፍ ብለን የጠቀስናቸው የህ-ብረተሰቡ የተለያዩ ክፍሎች ብሶታቸውን አንግበው በጋራ ሊነሱ ቀርቶ ተማሪውንና ወጣቱን በአንድነት፤ በአንድ ቀንና በአንድ መፈክር ከዳር እስከዳር በሃገሪቱ ከዚያም ወረድ ብለን በአዲስ አበባ ቢሆን ሁሉም ወጣት በአንድ ላይ እንዲነሳ ማድረግ የተቻለ አይመስልም። ይህ የሚያሳየን አንድ ቁም ነገር ነው። አመራር መስጠት ማለት ጥሪ ከመወርወር አልፎ ተማሪውና ወጣቱ ከዚያም በአሻገር ከፍ ብለን የጠቀስናቸው የተሰበጣጠሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ በተቀነባበረና በተደራጀ መልክ ተሰማርተው እነዚህ ክፍሎች በአንድነት እንዲነሱ ጥንቃቄ በተመላበት ሁኔታ ድርጅታዊ ስራ የሚሰሩ ጥቂትም ቢሆኑ የተዋቀሩ ዜጎች ያስፈልጋሉ ማለት ነው።

ሁለተኛ አመራር መስጠት ስንል በዚህ መልክ በአንድነት ለምንቀሰቅሳቸው የተለያዩ የህ-ብረተሰብ ክፍሎች ከነዚህ "ጥቃቅን" ከሚመስሉ የትግል መፈክሮች አልፎ የሚሄድና ለትግሉ ስኬታማ እልባት ብለን የምንጨብጠውንና የም-ንታገልለትን መፈክር ከወዲሁ በትግል ላይ ላለው ለህዝባችን ሳንታክት ለማስጨበጥ መስራት ይኖርብናል ማለታችን ነው። ይህ የትግላችን እልባት የም-ንለው ደግሞ በጣም ግልፅ ነገር ነው። የዚህ ሁሉ ጠብና መስዋእትነት መነሻ ወያኔ/ኢህአዴግ የህዝብ ድምፅ አላከብርም ብሎ አገዛዙን በመቀጠሉ እንደመሆኑ መጠን

ትግላችን በድል እልባት የሚያገኘው የህዝብ ድምፅ በነፃና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሚንፀባረቅበት ምርጫ በማዘጋጀትና የዚህ ምርጫ ውጤት የሚከበርበት መንገድ ሲመቻች ብቻ ነው። ይህንንም እስካሁን እንደተደረገው በአንድ መግለጫና ውሳኔ አማካኝነት ወርውሮ መተው የሚያዋጣ አይሆንም። እየተፋፋመ የሚካሄደው ትግል ዘላቂ አላማ የህብረቱ ሸንጎ ባሳለፈው ትክክለኛ ውሳኔ መሰረት ከእህአዴግ ቁጥጥር ውጭ በሆነና በተሙዋላ ዴሞክራሲያዊ አካባቢ በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ የሚል ነው። የምንታገለው ወያኔ/ኢህአዴግ በህዝብ ትግል ተዳክሞና ተገዶ በዚህ አጀንዳ ዙሪያ በሃቅ እንዲደራደር ለማድረግ ነው። በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ህዝባችንም ሆነ አለም አቀፉ ኮሙኒቲ ያለንን ተጨባጭ ፕሮፖዛል በግልፅ እንዲረዳው ለድርድር የምናቀርብቸውን ነጥቦች ግልፅ አድርጎ የሚያስቀምጥ እንደማኒፌስቶ አይነት ሰነድ በማውጣት ይፋ ማድረግ ይኖርብናል ማለት ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ብዙም የሚቸግር አይደለም። የድርድር አጀንዳ ብለን የምናቀርበው ሰነድ ከአንዳንድ መስተካከል ጋር ቀደም ሲል ባወጣነው የፖለቲካ ፕሮግራማችን ክፍል ሁለት የተጠቀሱትን ነጥቦች የሚቀየረውን ቀይሮ መጉላት ያለበትን አጉልቶ ማዘጋጀትና መበተን ይቻላል።

*በግንቦት 97 የምርጫ ሂደት ሳቢያ የተቀሰቀሰው ህዝባዊ ማእበል በወያኔ/ኢህአዴግ መጠን የሳተ አመፅ ብቻ ሳይሆን በአመራር ማጣት ከፍተኛ የመክሰም አደጋ ላይ ይገኛል። ያለንበት ችግር ወይም አጣብቂኝ የታጋይ መጥፋት አይደለም። በአመራር መጥፋት አንገቱን በመድፋት ላይ ያለው ህብረተሰብ በዚያው ልክ ደግሞ ከወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ጋር እልህ ወስጥ የገባ ይመስላል። ተነስ ተንቀሳቀስ የሚለው ሃይል እስካለ ድረስ ደግሞ ይህ እልህ ወደ ሃይለኛ የትግል ወኔ እንደሚቀየር መጠራጠር አይቻልም። አሁን በሃገራችን በሰፈነው የፖለቲካ ሁኔታ ያለውና የሚቀጥለው ከፍተኛ ቅራኔ በጠቅላላው ከዛሬ አመት ዛሬ በህብረተሰቡ ውስጥ ከሚንፀባረቀው ከፍተኛ የዴሞክራሲ ጥማት አንፃር በወያኔ/ኢህአዴግ በኩል ተጨማሪ ዴሞክራሲ ቀርቶ ከእንግዲህ አስራ አምስት አመት ሲመፃደቅ የቆየበትን የይስሙላ ዴሞክራሲ ፍንጭ እንኩዋን ለማረጋገጥ በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ አለመገኘቱ ነው። በኛ ግምት ይህ የማይታረቅ ቅራኔ ከእለት እለት እያሰፋ አነሰ የምንለው ዴሞክራሲ እየተቀነሰ ፍንዳታውን ከእለት እለት አይቀሬ እያደረገው እንደሚሄድ ግልፅ ነው።*

በዚህም የተነሳ መጭው ጊዜ በሚለፈፈውና በተጨባጩ በሚረጋገጠው ዴሞክራሲ መሃከል ያለው ክፍተት ከእለት እለት እየሰፋ ምንም አይነት ማስመሰል የማይችልበት ደረጃ ደርሶ ኢህአዴግ ''ነፃ ምርጫ አረጋግጣለሁ'' ብሎ በገፍ ሲያጭበረብር እንደተጋለጠው ሁሉ ''ዴሞክራሲም አሰፍናለሁ'' የሚለው ልፈፋ እንደዚሁ በግል-ፅ እየተጋለጠ የሚሄድበት ጊዜ እንደሆነ መተንበይ ይቻላል። ይህ የኢህአዴግ መሪዎች እርቃን የመቅረት ሂደት ብቻውን ቸር ወሬ ነው ሊባል አይችልም። በሚቀጥሉት ወራት መጠበቅ የሚቻለው የግፍና የአፈና ድርጊቶች እየተበራከቱ መሄዳቸውን ነው። የህዝባችን የዴሞክራሲ ጥማት የሚቀሰቅሰው ትግል እያየለ ከሄደ የኢህአዴግ መሪዎች አፈናና ፀረ ህዝብ ድርጊት ተያይዞ ይቀጥላል። አመራር አልባ ሆኖ ከቀዘቀዘና ህብረተሰባችን ትጥቁን የፈታ ከመሰላቸው ደግሞ ''አሸናፊነት'' እየተሰማቸው አፈናው፤ ማሳደዱ፤ ከስራ ማባረሩ፤ ግድያው ይቀጥላል። እንግዲህ በዚህ ባለንበት ተስፋ ሰጭም፤ ውስብስብም አስቸጋሪም ሁኔታ ከፊታችን አፍጦና አግጦ የሚደቀነው ጥያቄ ይህንን ትግል በምን አጀንዳ ማን ይምራው ያቀነባብረው የሚለው ጥያቄ ይመስለናል። ስለዚህ ነገሩን ሁለት ከፍሎ ማየት አንደኛ የትግል አጀንዳ ች-ግር ሁለተኛ የትግል አመራርና ቅንብር ችግር።

ትግሉ እያየለ ከሄደ ..ችግር
" ከቀዘቀዘ ...ተሰባችን

## 1ኛ. የትግል አጀንዳ ችግር

አጀንዳችን ባለው ተጨባጭ ሁኔታና አፈናን እየተቃወመና እየተቋቋቋመ እዛው በዛው ደግሞ ትግሉ በህዝባዊ ድል እልባት የሚያገኝበትን የድምፅ መከበር ጥያቄ ያነገበ ጥንድ አጀንዳ መሆን ይኖርበታል። ሁለቱ የሚነጣጠሉ አይደሉም።ከዚህ ሃቅ ከተነሳን በሚቀጥሉት ሳምንታትም ሆነ ወራት እያነሳን የምንቀጥልባቸው ጥያቄዎች ግልፅ ይሆኑልናል። ስትራቴጂያዊ አላማችንና ግባችን "የህዝቡ ድምፅ ይከበር" ነው። ሆኖም ይህ እንዳለ ሆኖ ለጊዜው ተንቀሳቅሰን ህዝባችንንም አለም አቀፍ ኮሙኒቲውንም የምንንቀሳቀስባቸው ጥያቄዎች ከፍ ብለን ከጠቀስነው የኢህአዴግ ከእንግዲህ የለየለትና ገሃድ አፋኝና ግፈኛ አገዛዝነት ጠባይ ጋር የተያያዙ ዝቅተኛና መሰረታዊ የመብትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ዙሪያ መሆን ይኖርበታል። በዚህ ደረጃ የምንጎናፀፈው ምንም ይሁን ምንም የድል ትንሽ አይኖረውም። ዜጎችን በደርዘን ሽህ እየቆጠሩ ማሰር በራሱ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ረገጣ ነው። ይፈቱ ብለን መታገላችን የዴሞክራሲያዊ ትግል አንድ አካል ነው። ዜጎችን በደርዘን ሽህ በማጎሪያ ሰፈር ማሰር፤ ሌሎች ቁጥራቸው ያልታወቀ ዜጎች ደብዛቸውን ማጥፋትና ዘመድ ወዳጅን ማሸበር የዝቅተኛ ዝቅተኛ የሆነውን ሰብአዊ መብት መርገጥ ነው። በግፍ የታሰሩ ዜጎች ይፈቱ ብለን እየታገልን ከዚያ ደግሞ "ዝቅተኛ" የሆነ ጥያቄ የኢህአዴግ መንግስት "ያሰራውን በይፋ አስርኩ ይበል! ሊስታቸውን ያውጣ! የታጎሩበትን ቦታ ለቤተዘመድ ያስታውቅ!" የሚሉት ጥያቄዎች አሁን ባለንበት ሁኔታ ለትግሉ ወሳኝ ጥያቄዎች ናቸው። ይህ ለወላጅና ለዘመድ አንገብጋቢ የሆነውን ያህል በዚያው ልክ ደግሞ የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ሊመልሱት በጣም የሚቸገሩበት ነገር ነው። አንገብጋቢና መሰረታዊ ጉዳይ በመሆኑ ዝም ተብሎ ከታለፈ ሌሎች በሽህ የሚቆጠሩ ዜጎችም ይህ እጣ ሊደርሳቸው ስለሚችል፤ በአለም አቀፍ ደረጃም "የዴሞክራቶቹ" የነመለስ ዜናዊ አመራር እርቃኑን የሚቀርበት ጥያቄ በመሆኑ እንደ ቁልፍ ጥያቄ ወስደን መንቀሳስ ይኖርብናል። የተገደሉትን ዜጎች ስም ማሳወቅ፤ የጅምላ መቃብሮችን መጠቆም፤ ከዚያ ወጥተው ዘመድ አዝማድ እርሙን አውጥቶ በስነ ስርአት እንዲቀብራቸው መጠየቅ፤ የተዘጉ ጋዜጦች ያለአንዳች ጫናና ቅድመ ሁኔታ መልሰው እንዲቋቋቋሙ ማድረግ....በሚሉት ጥያቄዎች መንቀሳቀስ ለወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች የማይዋጡም የማይተፉም ጥያቄዎች ናቸው።የማይዋጥ የማይተፋ ጥያቃ ማቅረብ ነው። በነዚህ ጥያቄዎች ወይ ድል ይገኛል ያኔ ደግሞ ለህዝቡ ወገኖች የድል በጎ አዙሪት ለወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ደግሞ የሚፈግፈግና የሽንፈት አስከፊ አዙሪት እምርታ የሚፈጥር አካሄድ ይሆናል። ወይ ደግሞ በነዚህ ዙሪያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች በአሻፈረኝነት ይቀጥላሉ ያኔ ደግሞ ከእለት እለት ይበልጥ እልህ እየገባ ከሚሄድ ህዝባዊ ትግል፤ ከእለት እለት ይበልጥ ልቡ እየተከፈለ የሚሄድ የኢህአዴግ የፖሊስና የመከላከያ ሰራዊት ከእለት እለት እየተጠየፋቸው ከሚሄድ አለም አቀፍ አካባቢ ውስጥ እየተዘፈቁ ስለሚሄዱ እዚህም ላይ የውድቀት አዙሪት ውስጥ ይገባሉ ማለት ነው።

ሆኖም ለነዚህ ለህዝብ መሰረታዊ መብቶች ቁልፍ ቦታ ሰጥተን የምናካሂደው ትግል ለአንዲት ሰከንድም ቢሆን የህዝባችንን ድምፅ ይከበር የሚል አጀንዳ መርሳት በጣም አደገኛ ይሆናል። አሁን አልፎ አልፎ እንደሚታየው ይህንን መሰረታዊ የህዝብ የትግል አጀንዳ "ለጊዜው" ወደ ጎን ትተን መሰረታዊ መብቶች ይከበሩ፤ የታሰሩት ይፈቱ በሚሉት መፈክሮች ብቻ አተኩሮ መታገል ከቀጠልን ብዙ ችግሮችና ፍረስትሬሽንስ ያጋጥሙናል። አንደኛ ነገር በነዚህ መሰረታዊ የመብት ጥያቄዎች ዙሪያ ትግሉ እያየለ ከቀጠለና የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ለማፈግፈግ ከተገደዱ ከፍ ብለን የጠቆምነው በህዝባዊው ሰፈር የበጎ በእነሱ ሰፈር ደግሞ የሽንፈት አዙሪት ተንቀሳቅሱዋል ማለት ስለሆነ የህብረተሰቡን ዴሞክራታይዜሽን ጥያቄ ከወዲሁ አያይዞ አለማቅረብ ህዝባችን ተሰውቶ በተጎናፀፈው ድል የሚፈጠረውን በጎ አዙሪት ከመጠቀምና ከመቀጠል ልንዝናጋ የምንችልበት ሁኔታ ይፈጠራል። ይህ ሁኔታ ከተፈጠረ የኢህአዴግ መሪዎች ይህንን ዳይናሚክስ ለመስበር የሚያስችላቸው ፋታ የምሰጥተበት አደገኛ ክፍተት ይከሰታል ማለት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ ፀረ ህዝቦቹ የተገኘውን ድል ሁሉ ጊዜና አጋጣሚ ጠብቀው መልሰው ሊቀሙን የሚችሉበት ሁኔታ ማመቻቸት ይሆናል። በአለም አቀፍ ኮሙኒቲውም "የተገኘው ድል ይበቃችሁዋል" በሚል ድጋፍ የምናጣበት ሁኔታ ይፈጠራል ወይም የመፈጠሩ አደጋ ይኖራል ማለት ነው።

2ኛ የፖለቲካ አመራር ስንል (3ኛ ያለውን የአመራር ክፍተት ለመሙላት....ካር በነዚህ የፖለቲካ አመራር ስንል ከፍ ብለን በጠቀስናቸው አንፃር ያሉ ጉድለቶች....)

2ኛ የፖለቲካ አመራር ስንል....

ህዝባችን ትግሉን አላቆመም። ያለው የአመራር፤ የአቅጣጫ ሰጭ የአቀነባባሪ ችግር ነው። በዚህ የአመራር ማጣት ጉዳይ ከግንቦት ወር ጀምሮ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት አን-ድ ቁም ነገር እንታዘባለን። ሚያዝያ ሰላሳ 1997 በቅንጅት ከተጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ወዲህ ላለፉት ዘጠኝ ወራት ህዝባችንን (ከጥሩምባ መንፋቱና ከሶስቱ ቀን የስራ ማቆም አድማ በስተቀር) ሰላማዊ ሰልፍ ወጥቶም ሆነ በሌላ ሰላማዊ ዘዴ ተቃውሞውን እንዲያሰማ በተቃዋም ድርጅቶች በኩል በይፋ የተጠራ አንድም እርምጃ የለም። ሆኖም ህዝባችን ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለቁጥር የሚታክቱ የተቃውሞ እ-ርምጃዎች ወስዱዋል። ብዙ መስዋእትነት የተከፈለባቸው ሰላማዊ ሰልፎች፤ ስራ ማቆም አድማዎች፤ ወዘተ የህዝብ ቁጣና የወያኔ ትንኮሳ እየተጋገዙ የጋበዙዋቸው ግብታዊ ተጋድሎዎች እንጂ በተቃዋሚ ድርጅቶች ጥሪ የተቀሰቀሱና የተመሩ አይደሉም። እነዚህ ህዝባዊ ተጋድሎዎች ከድርጅቶች አመራርና አነሳሽነት ውጭ ተካሂደዋል። አሁንም እየተካሄዱ ናቸው። ወደፊትም እንደሚቀጥሉ መጠርጠር አይቻልም። ነገር ግን የተደረገውም ሆነ በመደረግ ላይ ያለው የህዝብ መስዋእትነት ፍሬያማ እንዲሆን ከተፈለገ የግድ የፖለቲካ አመራር ያስፈገዋል። ያለውን አደገኛ የአመራር ክፍተት እነዚህን ህዝቡ በግብታዊነት እየተነሳሳ ያለአንዳች መመሪያ የሚያካሂዳቸውን ትግሎች አቅጣጫና ተጨባጭ መፈክር ማስጨበጥና ማቀነባበር የወቅቱ ዋናና አንገብጋቢ ተግባር አድርገን መውሰድ ይኖርብናል። ይህ ካልተደረገ ትግሉን የሚጠብቀው ችግርና አደጋ ግልፅ ነው። ፍሬው የማይታይ መስ-ዋእትነት መሰላቸት የማምጣት አደጋ ከመጋበዙ በላይ ትግሉ ያልተደራጀና ያልተጋገዘ ትግል እንደመሆኑ መጠን ይዋል ይደር እንጂ የተደራጀው የወያኔ/ኢህአዴግ ሃይል ሊያከሽፈው ይችላል። ከዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት ከተፈለገ ለዚህ ህዝባዊ ተጋድሎ አመራር ሰጥቶ ትግሉን ለድል ለማብቃት በሁለት አ)ጣጫ መንቀሳቀስ የግ-ድ ይሆናል። (ይህንን አይነቱን አመራር ማን ይሰጠው በሚለው ጥያቄ ስላለው ክሪዝ ዝቅ ብለን እንመጣለን ስላለው ክፍተት። መጀመሪያ ግን አመራር ስንል ምን ማለታችን ነው???) አመራር ስንል ሁለት ነገሮችን ለመጠቆም ነው። አንደኛ በያለበት ተራ በተራና በግብታዊነት የሚንቀሳቀሰውን ትግል በአንድነት እንዲካሄድ መጣር ማለት ነው። ይህ ደግሞ አመራር እሰጣለሁ የሚለው ሃይል የሚያነሳውን የትግል መፈክር ይመለከታል። በዚህ አሸባሪ አገዛዝ ላይ ብሶት ያለው ሁሉ በትግል ላይ ካለው ወጣቱና ዴሞክራት ጋር በአንድነት እንዲነሳ ልጆቻቸው የጠፉባቸው ወላጆች፤ ከስራ የተባረሩ ሰራተኞች፤ ነግዳቸው የታሸገባቸው ነጋዴዎች፤ ብሶታቸውን አንግበው በሌላ በኩል ደግሞ ሰብአዊ መብቶች ይከበሩ፤ ተጠያቂነት ይኑር፤ ነፃው ፕሬስ መታፈን ይብቃ፤ የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ....ወዘተ እያሉ በውጭም በውስጥም የህዝብን ብሶት የሚያስተጋቡ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች ሁሉ በአንድነት እንዲንቀሳቀሱ መጥራት ያስፈልጋል። ይህ እስካሁን ሲሞከር ቆይቱዋል። በህብረታችን ደረጃ እንኩዋን ደግመን ደጋግመን "የትግል አንድነት ጥሪ" "እስቸኩዋይ ጥሪ" ወዘተ እያልን ብዙ መግለጫዎች አውጥተናል፤ ብዙ ገለጣዎች አድርገናል። ነገር ግን እስካሁን እንደሚታየው ከሆነ እንኩዋን ከፍ ብለን የጠቀስናቸው የህ-ብረተሰቡ የተለያዩ ክፍሎች ብሶታቸውን አንግበው በጋራ ሊነሱ ቀርቶ ተማሪውንና ወጣቱን በአንድነት፤ በአንድ ቀንና በአንድ መፈክር ከዳር እስከዳር በሃገሪቱ ከዚያም ወረድ ብለን በአዲስ አበባ ቢሆን ሁሉም ወጣት በአንድ ላይ እንዲነሳ ማድረግ የተቻለ አይመስልም። ይህ የሚያሳየን አንድ ቁም ነገር ነው። አመራር መስጠት ማለት ጥሪ ከመወርወር አልፎ ተማሪውና ወጣቱ ከዚያም በአሻገር ከፍ ብለን የጠቀስናቸው የተሰበጣጠሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ በተቀነባበረና በተደራጀ መልክ ተሰማርተው እነዚህ ክፍሎች በአንድነት እንዲነሱ ጥንቃቄ በተመላበት ሁኔታ ድርጅታዊ ስራ የሚሰሩ ጥቂትም ቢሆኑ የተዋቀሩ ዜጎች ያስፈልጋሉ ማለት ነው።

ሁለተኛ አመራር መስጠት ስንል በዚህ መልክ በአንድነት ለምንቀሰቅሳቸው የተለያዩ የህ-ብረተሰብ ክፍሎች ከነዚህ "ጥቃቅን" ከሚመስሉ የትግል መፈክሮች አልፎ የሚሄድና ለትግሉ ስኬታማ እልባት ብለን

የምንጨብጠውንና የም-ንታገልለትን መፈክር ከወዲሁ በትግል ላይ ላለው ለህዝባችን ሳንታክት ለማስጨበጥ መስራት ይኖርብናል ማለታችን ነው። ይህ የትግላችን እልባት የም-ንለው ደግሞ በጣም ግልፅ ነገር ነው። የዚህ ሁሉ ጠብና መስዋእትነት መነሻ ወያኔ/ኢህአዴግ የህዝብ ድምፅ አላከብርም ብሎ አገዛዙን በመቀጠሉ እንደመሆኑ መጠን ትግላችን በድል እልባት የሚያገኘው የህዝብ ድምፅ በነፃና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሚንፀባረቅበት ምርጫ በማዘጋጀትና የዚህ ምርጫ ውጤት የሚከበርበት መንገድ ሲመቻች ብቻ ነው። ይህንንም እስካሁን እንደተደረገው በአንድ መግለጫና ውሳኔ አማካኝነት ወርውሮ መተው የሚያዋጣ አይሆንም። እየተፋፋመ የሚካሄደው ትግል ዘላቂ አላማ የህብረቱ ሸንጎ ባሳለፈው ትክክለኛ ውሳኔ መሰረት ከእህአዴግ ቁጥጥር ውጭ በሆነና በተመዋላ ዴሞክራሲያዊ አካባቢ በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ የሚል ነው። የምንታገለው ወያኔ/ኢህአዴግ በህዝብ ትግል ተዳክሞና ተገዶ በዚህ አጀንዳ ዙሪያ በሃቅ እንዲደራደር ለማድረግ ነው። በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ህዝባችንም ሆነ አለም አቀፉ ኮሙኒቲ ያለንን ተጨባጭ ፕሮፖዛል በግልፅ እንዲረዳው ለድርድር የምናቀርበቸውን ነጥቦች ግልፅ አድርጎ የሚያስቀምጥ እንደማኒፌስቶ አይነት ሰነድ በማውጣት ይፋ ማድረግ ይኖርብናል ማለት ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ብዙም የሚቸግር አይደለም። የድርድር አጀንዳ ብለን የምናቀርበው ሰነድ ከአንዳንድ መስተካከል ጋር ቀደም ሲል ባወጣነው የፖለቲካ ፕሮግራማችን ክፍል ሁለት የተጠቀሱትን ነጥቦች የሚቀየረውን ቀይሮ መጉላት ያለበትን አጉልቶ ማዘጋጀትና መበተን ይቻላል።

3ኛ ታዲያ ይህንን አመራር ማን ይስጠው??

ለዚህ ብቁ ሊሆኑ ይችሉ የነበሩትን ሃይሎች ተራ በተራ ብንቃኛቸው ዛሬ መሰረታዊ መብቶችን ለማስከበር ህዝቡ የሚያካሂደውን ትግል ለመምራትና ድምፅ ይከበር ለሚለው የህዝብ ትግል የተደራጀ አቅጣጫ ለመስጠት በሚለው አላማ ዙሪያ ግልፅ የሆነ የአመራር ክፍተት እንዳለ እናያለን። የህብረቱ የቀድሞ መሪዎች "የሰከነ ፓርላሜንታዊ ተቃውሞ" በሚል ሰበብ እጅ ከሰጡ ወዲህ እንኩዋን የህዝቡ ድምፅ ይከበር የመሰለን ከባድ አላማ ቀርቶ መሰረታዊ የህዝብ መብቶች ይከበሩ ለሚለው አጣዳፊ የህልውና ጥያቄ እንኩዋን ግፋ ቢል ከኢህአዴግ ጋር በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ አጋፋሪነት እንደራደር ይሉ እንደሆን እንጂ በነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ ህዝባዊ ትግሉን መቀስቀስም ሆነ መምራት የሚችሉበት ሁኔታ ውስጥ አይደሉም። የቅንጅቱ ችግር አመራሩ እንዳለ ታፍሶ እስር ቤት መግባቱና ተተኪ አመራር አለመፍለቁ ብቻ አይደለም። የድርጅቱ መሪዎች ፓርላማ ለመግባት ባቀረቡዋቸው ስምንት ቅድመ ሁኔታዎች በአለም አቀፍ ኮሙኒቲው አጋፋሪነት ከኢህአዴግ ጋር ተደራድረው በተለይ በፓርላማ የአሰራር ደንብ ጉዳይ ያቀረቡት ቅድመ ሁኔታ ተቀባይነት ካገኘ በድርጅት ደረጃ ወስነው በሙሉ ወይም አሁን እንደተያዘው እየተንጠባጠቡ ገብተው እነሱም እንደህብረቱ የመከፈል አደጋ ያጋጥማቸዋል። በየትኛውም ብንሄድ በሚቀጥሉት ሳምንታት በተቃዋሚው ጎራ በአንድ በኩል ፓርላሜንታዊ ተቃውሞ በሚሉና በሌላ በኩል ደግሞ ህዝባዊው የትግል ማእበል ይቀጥል በሚሉ ሃይሎች መሃከል ያለው ክፍፍል እየሰፋ ይሄዳል። ያለውን አደገኛ የአመራር ክፍተት ለመድፈንም ሆነ ለቀጣዩ ህዝባዊ ትግል ካለንበት አስቸጋሪ ሁኔታ የሚመጥን ስትራቴጂ ለመንደፍ ከፈለግን መጀመሪያ ስለዚህ ክፍፍል ግልፅ የሆነ የጋራ ትንተና መጨበጥና ይህንንም በጠቅላላው ለሃገሪቱ ዴሞክራቶችና በተለይ በሃገር ውስጥ ላለው ታጋይ ሃይል በሚገባ ማስጨበጥ ይኖርብናል።

ዛሬ በተቃዋሚው ጎራ (በተለይ ደግሞ በህብረታችን ውስጥ ነገ ደግሞ በቅንጅቱ ውስጥ የማይቀረው) የተፈጠረው ክፍፍል አንዳንዶች (ወያኔን ጨምሮ) ለማሳመን እንደሚፈልጉት በውጭ ባሉና በውስጥ ባሉ ዴሞክራቶች መሃከል ያለ ክፍፍል አይደለም። ያለው ልዩነት በአመዛኝ መልኩ የሚንፀባረቀው *እዛው አገር ቤት ውስጥ ነው።* በፓርላሜንታዊ ትግል ከተሰማሩት ጥቂቶች አንፃር የግንቦትን ድሎች ለማስከበር የሚደረገው ህዝባዊ ትግል ተቀጣጥሎና ተቀነባብሮ ይቀጥል የሚሉ እዛው አገር ቤት ውስጥ ያሉ የነዚሁ ድርጅቶች በርካታ አባላትና ሌሎች ስፍር ቁጥር የሌላቸው ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች አሉ። ያለው ክፍፍል በነዚህ በሁለት ሃይሎች መካከል ነው። በሃገራችን የተከሰተው የፖለቲካ ቀውስና አጣብቂኝ የህብረቱ አመራር ፓርላማ እንገባም ብሎ የወሰደው ውሳኔ

”ውጭ ያሉት” ውስጥ ባሉት ላይ በመጫናቸው የተከሰተ ችግር አይደለም። ቀውሱ አመራሮቹ በአጠቃላይ የኢትዮ ህዝብን ፍላጎት በተለይም ደግሞ በሃገር ውስጥ ያሉ አባላትን፤ በምርጫ ተወዳድረው በጭብርብር ተሸንፋችሁዋል የተባሉትንና መራጩን ህዝብ፤ የሃገር ሽማግሎችን፤ በየድርጅቱ ስር የተካተቱ የሴቶች፤ የወጣቶች፤ የገበሬዎች ተወካዮችን ሃሳብ በመቃረን ፓርላማ ለመግባት ወስነው ትግሉን አመራር አልባ በማድረጋቸው የተከሰተ ቀውስ ነው። በአለው የአፈና ሁኔታ በጥንቃቄ ለመራመድ ብቻ ሲባልና ከእሳት እራትነት ራስን ጠብቆ ትግልን በወኑ ለመምራት ባላቸው ጉጉትና ሃላፊነት ብቻ በመመራት ለጊዜው እዩን እዩን ባይሉም ቅሉ በነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ያሉ ብዙሃን የተወሰደውን እርምጃ እንደሚቃወሙና ህዝባዊ ትግሉን ከወጣቱና በአጠቃላይ ከህዝቡ ጎን ሆነው እንደዚሁም በውጭ ካሉ የድርጅቶቻቸው አባላትና ከህብረቱ አመራር እየመከሩ ለመስራት ቁርጠኛነት እንዳላቸው ከብዙ አቅጣጫዎች የሚደርሱን ጥቆማዎች ያረጋግጡልናል።

(ሊወጣ ይችላል ፅሁፉ እንዳይ.ረዝም.....). ያለው ተጨባጭ ሃቅ ይህ ሆኖ ሳለ በተለይ ኢህአዴግና የቀድሞው የህብረቱ መሪዎች ያለውን ክፍፍል “በዲያስፖራ ፖለቲከኞችና“ እዛው አገር ውስጥ ከተጨባጩ ሁኔታ እየተነሱ በሚታገሉ ሃይሎች መሃከል አድርገው ሲያቀርቡት ይህ አባባል ብዙ ቅን ወገኖችን ቢያሳስት፤ በአለም አቀፍ ኮሙኒቲውም አንዳን-ዶችን ሊያሳምን ቢችል የዚህ ም-ክንያቱ ግልፅ ነው። በሃገር ውስጥ ያሉት የህዝ--ብ ድምፅ እንዲከበር ህዝባዊ ትግል የሚሉት ብዙሃን ህዝባዊ አቋማቸውን ይዘው በይፋ ቢወጡ ለወያኔ ጭፍጨፋና አፈና ስለሚጋለጡ ለጊዜው ግራ የተጋቡ ሲመስሉ በሌላ በኩል ደግሞ ”የሰከነ ፓርላሜንታዊ ትግል” በሚል የህዝቡን ትግል አመራር የመስጠት ሃላፊነታቸውን ያስረከቡት መሪዎች በጠቅላላው በሃገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ካለው የሃይል ሚዛን አንፃር እጅግ አናሳ ቢሆኑም የያዙትን ኢህአዴግ የሚፈቅደውንና አለም አቀፍ ኮሙኒቲውም የሚያግዘውን ”የሰከነ ህጋዊ ተቃውሞ” አቋም እንደልብ ማስተጋባት መቻላቸው ካላቸው አቅምም ሆነ ህዝባዊ ቅባሉት ጋር ምንም ግንኙነት በሌለው መልክ ጎልተው የመታየት እድል ሰጥቱዋቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የቀድሞው የህብረቱ መሪዎች ያለውን ልዩነት “በውጭና በውስጥ“ ባሉት መሃከል አድርገው ሲያቀርቡት ለዚህ ማወናበድ የሚያግዛቸው ሌላ ክስተት አለ። ይኸውም በውስጥ ያለው ታጋይ በአለው አፈና ምክንያት ይፋ ወጥቶ በማይታይበት ሁኔታ በውጭ ህዝባዊ ትግል ለህዝባዊ አጀንዳ ብሎ የሚንቀሳቀሰው ሃይል ጎልቶ ለመታየት በመቻሉ ነው።

ከዚህ ሁሉ ስንነሳ ለህዝባችን ትግል መቀጠል ሲባል ይህንን መዛባት ለማስተካከል ከፈለግን ከአንድ መሰረታዊ ሃቅ ተነስተን ወደ አንድ መደምደሚያ ብቻ እንደርሳለን። መሰረታዊው ሃቅ ህዝባችን በሃገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን የቀድሞ መሪዎች ረስቶ ከነሱ ምንም የረባ ነገርም ሆነ አመራር ሳይጠብቅ ትግሉን በግብታዊነት ህያው አድርጎ እስካሁን መቀጠሉ ነው። በሃቅ ነገሮችን ለሚተነትን ማንም ታዛቢ ይህ ሁኔታ ብቻውን ክፍፍሉን በውጭና በውስጥ አድርጎ ለማቅረብ የሚሞከረውን ሁሉ የሚንድ ተጨባጭ ክስተት ነው። በዚህ ላይ ገን-ብተን የህዝባችንን ትግል መልክ አስይዘን ለድል እናብቃው ካልን ደግሞ ከዚህ ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተን የምንደርስበት ድምዳሜ አንድ ብቻ ይመስለናል። ለህዝብ አጀንዳ በህዝብ ትግል የሚሉት በውስጥም በውጭም ያሉ ሃይሎች ተፈላልገው፤ ተገናኝተውና ተቀነባብረው የሚሰሩበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል። ለዚህ ደግሞ ሃህብረታችን እዛው አገር ቤት የህቡእ መዋቅሩን በህብረቱ አባል ድርጅቶችና በተለያዩ በትግል ላይ ባሉ የህብረተሰብ ክ-ፍሎች ዘርግቶ መንቀሳቀስ መጀመሩ ይደር የማይባል አን-ገብጋቢ ተግባር ነው።

1ኛ ጥያቄ

1ኛ ጥያቄ - ይህንን ትግል ማን ይምራው?

አሁን ባለው ተጨባጭ የሃገሪቱ ሁኔታ ለዚህ ሊኖር የሚችለው መልስ አመራሩ ከውጭ የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት የሚለው ብቻ ነው። በሃገራችን በመካሄድ ላይ ያለው ትግል በአብዛኛው የአለም አገሮች ከሚካሄድ ማንኛውም አይነት የፖለቲካ ትግል ለየት ያለ መልክ አለው። ህዝብን ለትግል ለመቀስቀስ፤ ተነስ ታገል እያሉ በውስጡ ተተክሎ ለመንቀሳቀስ የግድ የሚልበት ማለትም የግድ በውስጡ ሆኖ አመራር ለመስጠት የማያስፈልግበት ሁኔታ ውስጥ ነን። በኬንያ ወይም በዩጋንዳ፤ በሃይቲ ወይም በሌላ ማንም አገር ከሚደረግ ትግል ይልቅ ዛሬ በወያኔ/ኢህአዴግ ኢትዮጵያ የሚደረገው ትግል ይበልጥ ሊመሳሰል የሚችለው በዘረኛው አገዛዝ ስር በደቡብ አፍሪካ ከተካሄደው ፀረ አፓርታይድ ትግል ጋር ነው። በዚች አገር ልክ አሁን በኛ አገር እንዳለው ሁኔታ ህብረተሰቡ በነቂስ ያለውን ስርአት ተቃውሞ ለመታገል ዝግጁ ስለነበረ ከአመራሩ ሁለት ሶስተኛው እስር ቤት ሆኖ የቀረው ደግሞ ለስደት ተዳርጎ ትግሉ ለመቀጠል ተችሏል። በኛም አገር ከዚህ ትምህርት የቀሰመ ስልት እናውጣ ካልን ሁለት ተጓዳኝ እርምጃዎች መውሰድ ይኖርብናል። በአንድ በኩል አሁን በተለያዩ ምክንያቶች አመራር ጠፍቶ በአደገኛ ሁኔታ በመፋዘዝ(???) ላይ ካለው የትግል ሁኔታ ለመውጣትና ትግሉ እንደገና በሃገር ውስጥ ባለ አመራር ለመመራትና ለማንሰራራት እስኪቻል ድረስ በእነ መቶ አለቃ አያል ሰው በቀረበው ሃሳብ መሰረት ከተለያዩ የፖለቲካና ሌሎች ሃይሎች የተዋጣ አንድ ጊዜያዊ የሆነ የቀውጢ ወቅት የጋራ አካል ተቋቁሞ የትግሉን አመራር መረከቡን ይፋ ማድረግ ያስፈልጋል። ሁለተኛ በሃገር ውስጥ የይፋ ትግል መስክ እየጠበበ ቢሄድም በተቻለ መጠን ዜጎች በይፋና ህጋዊ ዘዴ እንዲንቀሳቀሱ እያበረታቱ በዚያ ተጓዳኝ ደግሞ ከውጭ ካለው አካል ጋር እየተገናኘ የሚሰራ አንድ የህቡእ መዋቅር መዘርጋት እጅግ አስፈላጊ ይሆናል።

## 3ኛ. እንዴት እንንቀሳቀስ?

ለጊዜው የትግሉን አመራር ከውጭ አድርገን እንንቀሳቀስ ካልን የምንመርጣቸው የትግል ስልቶች እዛው ሃገር ቤት ህዝቡ ውስጥ ተተክሎ ከሚደረጉ ጥሪዎች ለየት ያሉ ይሆናሉ። በዚህ ላይ ሁለት ነጥቦች ማንሳት ይቻላል።

አንደኛ የምናቀርበው ጥሪ የሲቪል ዲስኦቢዲያንስ ጥሪ ቢሆንም በህዝቡ ውስጥ ተተክለን ልንቆጣጠረው የማንችለው ትግሉንና ህዝቡን ለኢህአዴግ ትንኮሳ ከሚያጋልጡ የትግል ጥሪዎች መቆጠብ ያስፈልጋል። ለምሳሌ አሁን ባለንበት ደረጃና ቀስ በቀስ እያደገ በሚሄደው ትግል አመራር እስኪፈልቅ ድረስ ሰላማዊ ሰልፍ መጥራት እስከዚህም የማያዋጣ ሊሆን ይችላል። የምንሰማራበት የትግል ስልት "አክቲቭ" ሊባል ከሚችል ስልት ይልቅ ፍጥጫን ወይም (ኮንፍሮንቴሽን) ጋብዞ ህዝባችንን አደጋ ላይ የማይጥል "ፓሲቭ" የሆነ ለጊዜው ለምሳሌ እንደ ርሃብ አድማ አይነቱ ስልት ይበልጥ ተስማሚ ይመስለናል። ለምሳሌ ዛሬ ትግሉን እንደገና ለመቀስቀስ ከፍ ብለን ባነሳነው የታሰሩ ወጣቶች ስም ዝርዝር ይመዝገብ፤ የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት ይፋ ያድርግ በሚል ጥሪ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የርሃብ አድማ እንዲመቱ ጥሪ ማድረግ ይቻላል።

ሁለተኛ ደግሞ ይህንን ጥሪ ከውጭ ሆነን የምናደርገው ስለሆነ ይበልጥ ተአማኒነት የሚኖረው በውጭ ያሉ ዜጎችም ሲሳተፉበትና ለሃገር ውስጡ አርአያ ሲሆኑ ነው። በመሆኑም ይህንን አድማ ለመጥራት ውሳኔ ከተደረገ ጥሪው በመላ አለም ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሆኖ እንዲያውም በአለም ዋና ዋና ከተሞች (ለንደን፤ ዋሽንግተን ...) በርካታ ዜጎች የሚሳተፉበት አድማ ከሃገር ቤቱ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ እንዲጀምር ማድረግና ወደ ሃገር ቤት በሰፊው እንዲስተጋባ ማድረግ ያስፈልጋል።

1. ያለንበት አጣብቂኝ

ከህብረቱ ውሳኔ ውጭ የሃምሳ ሰዎች ፓርላማ መግባትና የህዝቡን ትግል በነሱ ፓርላሜንታዊ ትግል ለመተካት መሞከር ሲደረግ ይህንን ተቃውመው የህዝቡ ትግል ይቀጥል የሚሉት ብዙሃን መንቀሳቀስ የሚችሉበት ሁኔታ ውስጥ አይደሉም። ፓርላማ የገቡት ደግሞ ወያኔ ከሚፈቅደው በላይ ተቃውሞ ማሰማት ስለማይችሉ እንኳዋን የህዝቡ ድምፅ ይከበር የሚለውን ትግል ሊመሩና ሊያስተባብሩ ቀርቶ ሰሞኑን የሚደረጉትን አፈናዎች እንኳዋን

በመግለጫ ደረጃ የሚቃወሙበት ሁኔታ ውስጥ አይደሉም።

2. ያለው ክፍፍል

3. ያለው ውዥንብር

የህብረቱ አመራር ፓርላማ አንገባም ብሎ የወሰደው ውሳኔ "ውጭ ያሉት" ውስጥ ባሉት ላይ የጫኑት ውሳኔ አይደለም። በአጠቃላይ የኢትዮ ህዝብ፤ በተጨባጭ ደግሞ የህብረቱ አባላትና ደጋፊዎች (ተወዳዳሪዎች) ነው። የተፈጠረው ቀውስ እስከዚህም አመራሮቹ የህብረቱን የጋራ ውሳኔ ከመጣሳቸው የመጣ ሳይሆን የኛን በሃገር ውስጥ ያለን አባላትን፤ የሃገር ሽማግሎችን፤ በየድርጅቶቻችን ስር የተካተቱ የሴቶች፤ የወጣቶች፤ የገበሬዎች ተወካዮችን ሃሳብ በመቃረን ፓርላማ ለመግባት ወስነው ትግሉን አመራር አልባ በማድረጋቸው የተከሰተ ቀውስ ነው። (የነ አካሉን ማየት) በአለው የአፈና ሁኔታ በጥንቃቄ ለመራመድ ብቻ ሲባልና ከእሳት እራትነት ራስን ጠብቆ ትግልን በወጉ ለመምራት ባለን ጉጉትና ሃላፊነት ብቻ በመመራት ለጊዜው ዝምታን ብንመርጥ በነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ያለን ብዙሃን የተወሰደውን እርምጃ እንደምንቃወምና ህዝባዊ ትግሉን ከወጣቱና በአጠቃላይ ከህዝቡ ጎን ሆነን እንደዚሁም በውጭ ካሉ የድርጅቶቻችን አባላት እየመከርን ለመቀጠል ቁርጠኛነት እንዳለን ሊታወቅ ይገባል።

4. ስላለው ውስብስብና አስቸጋሪ ሁኔታ

5. ስላለው የትግል ስልት አማራጭ

የህዝቡን ሰላማዊና ህጋዊ ትግል የህገወጥ አመፅ ጥላሸት ለመቀባትና ፀአሳዳሪዎቹ ፊት በመተከል ላይ ያለውን የሽብር አገዛዝ ሰበብ ለማግኘት ታጣቂ ቢያጣ የራሱን ታጣቂዎች በህዝቡ መሃከል እያሰረገ፤ አሸባሪ ቢያጣ በራሱ አሸባሪዎች ብምብ እየወረወረ በህዝብ ተተፍቶ አገዛዙን ለመቀጠል ከህገ ወጥና ከአመፅ ሌላ ምንም ያልቀረው ሃይል ጋር በትንንቅ ላይ ነን። የትግል ስልትን በተመለከተ ምርጫ የሌለው የወያኔ/ኢህአዴግ አመራር ብቻ ነው። ከሰላማዊና ህዝባዊ ትግል በስተቀር አማራጭ እምብዛም የለንም።